# የአገር መከላከያ ሰራዊት የሶማሊያ ተልእኮውን በተሳካ አኳኋን አጠናቆ መውጣት መጀመሩን በማስመልከት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ መግለጫ

የኢፌዲሪ የአገር መከላከያ ሰራዊት ከሁለት አመት በፊት በሶማሊያ ውስጥ የበላይነት ማግኘት ጀምረው የነበሩ አክራሪ ሃይሎች በተደጋጋሚ በኢትዮጵያ ላይ ያወጁትን የጂሃድ ጦርነትና የደቀኑትን ወቅታዊና ተጨባጭ አደጋ ለማክሸፍ ወደ ሶማሊያ መግባቱ ይታወሳል። ሰራዊቱ በአገራችን ላይ ተደቅኖ የነበረውን አደጋ በአጭር ጊዜ በማስወገድ የመጀመሪያውንና ወሳኙን ተልእኮውን በተሳካ አኳኋን ፈጽሟል። የአገር መከላከያ ሰራዊት ይህን ወሳኝ ተልእኮ በተሳካ ሁኔታ በመፈፀሙ ወዲያውኑ ወደ አገሩ እንዲመለስ ማድረግ ይቻል የነበረ ቢሆንም ወንድም የሆነው የሶማሊያ ህዝብ በተፈጠረለት መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ ከመንግስት አልባነት ወደ ተደራጀ መንግስታዊ ህልውና ሊያመራ እንዲችል እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ እዚያው በመቆየት ድጋፍ መስጠት እንዳለብን ታምኖበት ሰራዊታችን ለሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት የሚበጅ ስራ እየሰራ እንዲቆይ በመወሰኑ ከሽግግር መንግስቱ ጋር በመሆን ለሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት በከፍተኛ የሃላፊነት መንፈስ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል።

አገራችን ባለፉት ሁለት አመታት በሶማሊያ ውስጥ ሰራዊቷን በማቆየት ለሰላምና መረጋጋት እንዲሰራ በማድረግ ሳትወሰን የአፍሪካ ህብረትና መላው አለም አቀፍ ማህበረሰብ ለጉዳዩ በቂ ትኩረት ሰጥቶ የሶማሊያን መረጋጋት እውን ለማድረግ ሚናውን እንዲጫወት አስፈላጊውን ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች። ኢትዮጵያ በተናጠልም ሆነ በኢጋድና በአፍሪካ ህብረት አባልነቷ ባካሄደችው ሰፊ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ለሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት አለምአቀፋዊ የአቋም ድጋፍና በተወሰነ ደረጃም በአፍሪካ ህብረት በተለይም በቡሩንዲና በኡጋንዳ ተጨባጭ እንቅስቃሴ የሚገለጽ ድጋፍ ለማስገኘት ችላለች።

ኢትዮጵያ በሶማሊያ ከሽግግር መንግስቱ፣ ከሶማሊያ ህዝብና ከአፍሪካ ህብረት የሰላም አስከባሪ ሃይሎች ጋር በመሆን ለሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት የሚበጁ በርካታ ተግባራትን አከናውናለች፡፡ የማታ ማታ ደግሞ ሂደቱ በሶማሊያ ውስጥ ያሉ ሰላም ወዳድ የፖለቲካ ሃይሎችን የሚያሳትፍ ሰፊ መሰረት ያለው የሽግግር ሂደት እንዲሆን መደረግ እንዳለበት ታምኖበት ራሳቸውን ከአክራሪ አቋም ባላቀቁ የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች አባላትና የሶማሊያ የሽግግር መንግስት መካከል ጅቡቲ ላይ ድርድር ተካሄዶ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ በሶማሊያ ሰላማዊ የፖለቲካ ሃይሎች መካከል ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ የድርድር መድረክ ላይ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እ.ኤ.አ. በ2008 ማብቂያ ላይ ሶማሊያን ለቆ እንዲወጣ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

በዚህ መሰረት የአገር መከላከያ ሰራዊት የሶማሊያ ተልእኮውን አጠናቅቆ የሚወጣበት እቅድ ከተዘጋጀ በኋላ ባሳለፍነው የፈረንጆች አመት ማብቂያ ላይ ይህንኑ የመውጣት እቅድ ተግባራዊ የማድረግ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡ ሰራዊታችን ከሶማሊያ ለቆ በሚወጣበት ጊዜ ክፍተት እንዳይፈጠርና የሶማሊያ የፀጥታ ሁኔታ እንዳይባባስ የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር ቀደም ሲል ጀምሮ ሲካሄድ የነበረውን ስራ በማጠናከር የመጨረሻ ምዕራፍ ተግባራቱን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ይህን ተግባር በተሟላ መግባባት ለማጠናቀቅ ይቻል ዘንድ የአሚሶም ሃይሎች አዛዥ፣ የሽግግር መንግስቱ ታጣቂዎች አዛዥና በሶማሊያ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሰራዊት አዛዥ አዲስ አበባ ላይ ተገናኝተው የመጨረሻውን ዝግጅት እንዲገመግሙና ቀጣይ ተግባራትንም እንዲነድፉ ተደርጓል፡፡ የአሚሶምን ሃይሎች ለማጠናከር የዩጋንዳና የቡሩንዲ መንግስታት ተጨማሪ ሃይል ለማስገባት ዝግጁ መሆናቸው የተረጋገጠ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት የሶማሊያ ተልእኮውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቆ የሚመለስበት የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሷል፡፡

ይህን መሰረት በማድረግ የሽግግር መንግስቱ ታጣቂዎችና የአሚሶም ሃይሎች በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ይሸፈኑ የነበሩ አካባቢዎችን እንዲረከቡ ተደርጓል፡፡ የሞቃዲሾና ሌላው የሶማሊያ ህብረተሰብም በተደራጀ አኳኋን ሰላሙን እንዲያስጠብቅና እንዲያሰፋ ላለፉት ሁለት አመታት ሲሰራ የቆየውን ስራ በማጠናከርም አስፈላጊው ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

እነዚህ ተግባራት መከናወናቸው ከተረጋገጠና የአሚሶም ሃይሎች በሶማሊያ ለመቆየት ያላቸውን ዝግጁነት በተግባር ካሳዩ በኋላ መንግስት ከዚህ ቀደም በገባው ቃል መሰረት የመከላከያ ሰራዊቱ ከሶማሊያ ለቆ እንዲወጣ በማድረግ ላይ ይገኛል። ሰራዊታችን ከሶማሊያ የሚወጣበት አግባብ የጥቂት ቀናት ሂደት እንጂ ቅፅበታዊ በሆነ ጥድፊያ የማይፈፀም በመሆኑ የተጀመረው ሶማሊያን ለቆ የመውጣት እንቅስቃሴ በተቻለ ፍጥነት በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት እንዲጠናቀቅ ይደረጋል።

የኢፌዴሪ መንግስት በሶማሊያ ዘላቂ ሰላም የማስፈን አስፈላጊነት ዛሬም ያልተመለሰ የህዝብ ጥያቄ እንደሆነ በመገንዘብ አለም አቀፍ ማህበረሰብ ለጉዳዩ ይበልጥ ትኩረት ሰጥቶ ሶማሊያን ከቀውስ  ለማዳን ሃላፊነቱን በሚገባ እንዲወጣ ጥሪውን ያቀርባል። የአፍሪካ ህብረትና የኢጋድ አባል አገሮች በተለይም ለሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት ተጨባጭ አስተዋፅኦ ለማበርከት ሰራዊታቸውን በሰላም አስከባሪነት የላኩ የዩጋንዳና የቡሩንዲ መንግስታትና ህዝቦች አፍሪካዊ ተልእኳቸውን ለመወጣት በማሳየት ላይ ላሉት ፅኑ አቋምና ተግባር ያለውን ከፍተኛ አድናቆትም ይገልፃል። የመከላከያ ሰራዊታችን በአገራችን ላይ ተደቅኖ የነበረውን ወቅታዊና ተጨባጭ አደጋ በማስወገድ የተሳካ ስራ ከመስራቱ በተጨማሪ ላለፉት ሁለት አመታት በሶመሊያ ውስጥ በመቆየት አክራሪዎችን ለማዳከምና ለሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት ለከፈለው መስዋእትና ላበረከተው አስተዋፅኦ በመላ የአገራችን ህዝቦችና በኢፌዴሪ መንግስት ስም ያለውን አድናቆት እየገለፀ ኢትዮጵያ ዛሬም እንደትላንቱ በሶማሊያ መረጋጋትና ሰላም ላይ ያላትን ፅኑና ልባዊ አቋም በተግባር እያሳየች እንደምትቀጥል በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ ያረጋግጣል።

ታህሳስ 25 ቀን 2001 ዓ.ም